# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (አሀ! አሕ! ኢሕን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 1 ቁጥር 2 ጥቅምት ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም.

## የወያኔ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መቀበሪያው ይሆናል

የኢሕአዴግ/ህወሀት አገዛዝ የጥፋት አዋጅ አውጇል። ይህ በሀገርና ሕዝብ ላይ “በአስቸኳይ ጊዜ” ስም የታወጀ አውዳሚ አዋጅ የወያኔ/ህወሀት መጥፊያው እንደሚሆን መናገር ይቻላል። በዓለም ደረጃም ይሁን በሀገራችን አምባገነን ገዥዎች በባህሪያቸው ተመሳሳይ ናቸው። ካልተዋረዱ በቀር ሥልጣናቸውን አይለቁም። ሕዝባዊ ማዕበል ካልዋጣቸው በቀር ከሥልጣን ሊወገዱ አይችሉም። ሕዝብን ለመግዛት፣ የሀገርን ሀብት ለመዝረፍ በወታደራዊ ኃይላቸው ይጠቀማሉ። ስለ መብት፣ ስለ ነፃነት ድምጹን የሚያሰማውን ሁሉ ተቀጥላ ስም በመስጠት ያስራሉ፣ ያሰቃያሉ፣ ይገድላሉ። በሕዝብ ላይ ለመከመር ሲሰብኩና “ታገልንለት” ሲሉ የነበረውን “ዴሞክራሲያ መብት” ስልጣኑን ከያዙት በኋላ ሊሰሙም አይፈልጉ። በሀገርና በሕዝብ ስም ለመነገድ ዋነኞች ናቸው። ሀገር ማለት እነሱ እስከመሩትና እስከአስተዳደሩት ብቻ ነው። ምን ዓይነት መንግሥትና አስተዳደር ገልብጠው እንደመጡ ዞር ብለው አይመለከቱም። በጥቅሉ ከአለፈ ታሪክ አይማሩምና ወደ ከርሰ መቃብራቸው የሚከታቸው ሕዝባዊ ማዕበል ነው።

ወያኔ/ህወሀት የ25 ዓመት የአገዛዝ ታሪኩ ኢትዮጵያን ማዳከም፣ ሕዝቧን መከፋፈል ለመሆኑ ተደጋግሞ ተጽፏል፣ ተነግሯል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ዘረኛ አገዛዝ ለ25 ዓመታት ተሸክሟል። ሕዝባችን በወያኔ አገዛዝ እንጀራ በሽሮ ናፍቆታል፣ እንኳን የቡና ቁርስ የዕለት ቁርሱን አጥቷል፣ ምሳና እራት አጣምሮ እንዲበላ ተገዷል። ህሊናን በሚሰቀጥጥ አኳያ የመንግሥት ሠራተኞች ገልመጥ፣ ገልመጥ ብለው የተቀቀለ ድንችና ሳምቡሳ ምሳ አድርገው ይውላሉ። ሕፃናት ቁርስ ሳይቀምሱ ወደ ትምህርት ቤት ይላካሉ። በየመንገዱና በየትምህርት ቤቱ ተዝለፍልፈው ወደ ቤታቸው የሚመለሱ ሕፃናት በርካታ ናቸው። ከምግብ ማጣት ትምህርታቸውን አቋርጠው ቆሎ ሻጭ፣ መጽሐፍና ሎተሪ አዟሪ፣ ሊስትሮ ወዘተ. በመሆን ለቤተሰቦቻቸው ትርፍራፊ ምግብ ይዘው የሚገቡ በርካታ ናቸው። በየመንገዱ ለወያኔ ባለስልጣናትና የጊዜው ሀብታሞች እንሰሳዊ ባህሪ መጫወቻ የሆኑ እህቶቻችን የወያኔ አገዛዝ ውጤቶች ናቸው። ከሥራ ማጣት የተነሳ በየአካባቢው “ጉልበተኛ” ዕቃ ጫኝና አውራጅ በመሆን፣ በየታክሲ መሳፈሪያው በተራ አስከባሪነት የተበራከቱ ወጣቶች ሆን ተብሎ ህብረተሰቡን ያውኩ ዘንድ “ፍንዳታና ወያላ” በሚል ስያሜ የወደፊት ዕጣ ፈንታቸው የደበዘዘ ወጣቶች በወያኔ “ትውልድ የመቅበር” ዕቅድ ዒላማዎች ናቸው።

ዕቅድና ዝግጅት ሳይኖረው በተለይ በአዲስ አበባ ነዋሪ ላይ የማፈናቀል ዘመቻ ወያኔ ሥልጣን ከጨበጠ ጀምሮ ሲያካሂደው የነበረው ፖሊሲ ነው። በኃይልና በጉልበት የመኖሪያ ቄያቸው በግሬደር እየተደረመሰ መግቢያ ያጡ ቤተሰቦች በርካታ ናቸው። በየአካባቢው በዕድር መልክ ተሰባስቦ ያለውን፣ እንደ ባህሉ የሚረዳዳውን ህብረተሰብ ግንኙነት ለመበጠስ ከኖረበት ቀዬ እያፈናቀሉ ለእራሳቸውና ለወቅቱ ዘራፊዎችና ባዕዳን ቦታውን የሚቸበችቡ ወያኔዎች ስንቱን እንዳስለቀሱና

*የላስቲክ ቤት ተጠቃሚ እንዳደርጉ ቤቱ ይቁጠረው። ፊትበር፣ መገናኛ፣ ኮልፌ፣ ጨርቆስ፣ ጎፋ ሠፈር፣ አራት ኪሎ፣ ካዛእንችስ፣ አዋሬ፣ በቅሎ ቤት፣ ወሎ ሠፈር፣ ወዘተ ወዘተ ዛሬ ታርሰዋል። ከተማዋን ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶች ለሚፈናቀለው ኅብረተሰብ ለየዕለት ኑሮው አስፈላጊውንና መሠረታዊ ጉዳዮችን ሳያሟሉ የማካሄዱ ውጤት በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ቤተሰቦች የወያኔን መውደም እንዲመኙ አድርጓል። ለዘመናት ከኖሩበት አካባቢ እርቀው እንዲሠፍሩ የተደረጉ ቤተሰቦች ልጆቻቸው ከትምህርት ቤታቸው እጅጉን በመራቃቸው ለቀን ሥራና ለሌብነት የተዳረጉ በርካታዎች ናቸው። የአካባቢ መገበያያ ጉልታቸው የየዕለት ችግራቸው መደጎሚያን አውድሞ ኅብረተሰቡን የመበተን ውጤት "እግዚአብሔር ጉዳቸውን አሳየኝ" ባዩ ይበራከት ዘንድ ያስመዘገበው ውጤት ነው።*

*በተመሳሳይ መልኩ በአዲስ አበባና አካባቢዋ ያሉትን አርሶ አደሮች እንደ ዕቃ በመወርወር ለም መሬታቸውን ለውጭና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የቸበቸበው ወያኔ በገጠሩ ነዋሪ ቢጠላ ምን ይገርመዋል። በጥቅሉም በሀገሪቷ ያሉትን ለም ቦታዎች የንዋይ ጥማታቸውን ለማርካትና ሀገሪቷን ከውጭ ባለሀብቶች ጋር ውስብስብ ችግር ውስጥ ለመክተት በየክፍላተ ሀገሩ የአርሶ አደሩን ከእርሻውና ከቀዬው እያፈናቀሉ በሀገሩ መኖሪያ እስኪያጣ የተፈጸሙ በደሎች ውጤቱ ሕዝብ ወያኔ ላይ ማመጽ ቢሆን ምን ያስገርማል። በፈጠረውም የዘረኝነት ፖሊሲ እንደ ንዋይና ንብረት ክልል ዘረፋ የገባው ወያኔ የወልቃይትና የጎንደር ሕዝብ "ዓይንህ ለአፈር"፣ የኦሮሞ ልጆች "ዳውን ዳውን ወያኔ"  ቢሉት ይገባዋል።*

*በየጤና ጣቢያው የተኮለኮለው ሕመምተኛ፣ በየሆስፒታሉ መዳን ሲችሉ የሚረግፉት አዛውንት፣ ሕፃናትና ወጣቶች በወያኔ ቢያማርሩ ምን ይደንቃል። የሚዘርፉትን ገንዘብ ምን እናድርገው ባዮች በየመጠጥ ቤቱና ምግብ ቤቱ አልበቃ ብሏቸው ጎሊናቸውን ሲስቱ "ስለ እግዚአብሔር፣ ጋሽዬ ራበኝ፣ ..." ባዩ እጁን ዘርግቶ ሲማጸናቸው፣ ለትርፍራፊያቸው ሲተራመስ ማየቱ ከሞት አይሻል ሕይወት የተቸረው ኅብረተሰብ "ወያኔ ይውደም!" ቢል ምን ያስደንቃል።*

*ወያኔ የሀገርና ሕዝብ ፍቅር የለውምና ሕዝብን እያሰቃየ፣ የሀገር ሀብት እየዘረፈና እያዘረፈ 25 ዓመት አስቆጥሯል። የወያኔ ግፍ ሞልቶ ፈሷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትዕግስቱ ተሟጧል። በረሃብና በችግር እየተገረፈ ያለው ኅብረተሰብ በዘርና በሃይማኖት ይጋጭ ዘንድ የከፋፍለህ ግዛ ዕቅዱ የጣለው ጠባሳ ቀላል ባይሆንም  ዛሬ ወያኔ ላይ ሁሉም ጣቱን ጠቁሟል። ሀገር ለሕዝብ እንድትሆን፣ ሕዝብ የዜግነት መብቱን እንዲያገኝ መፍትሄው የወያኔ/ህወሀት መውደም ብቻ እንደሆነ ከማንም በላይ የተረዳው የመከራውና የግፉ ተቋዳሽ ኅብረተሰብ ከእንግዲህ ለወያኔ አይገዛም።*

*የአምባገነኖች የመጀመሪያም የመጨረሻም በትር ግድያ ነውና በረሃብ፣ በጤና፣ በስደት ወዘተ ሕይወቱን እያጣ ያለው ኅብረተሰብ ዛሬ ወያኔን ቀብሮ ሊሰዋ ተነስቷል። ወንጀለኛ፣ ገዳይ፣ ፋሽስት፣ ሥርዓት መጠገን ሳይሆን መውደም ነው ያለበትና የሚከፈለው መስዋዕትነት ተከፍሎ ድል ለሕዝብ እንዲሆን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (አሀ! አሕ! ኢ.ሕን)" ከሕዝባችን ጎን መሰለፋችንን ልንገልጽ እንወዳለን።*

*የወያኔ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመጨረሻው የኑዛዜ አዋጅ እናደርገዋለን። በዚህ አሸባሪ የወንበዴ አገዛዝ የሚሸበር ልብ፣ የሚንቀጠቀጥ ሰውነት አይኖርም። 25 ዓመት ሙሉ ሲዋሽና ሲያስፈራራ የኖረው ወያኔ ማንነቱን ይበልጥ እያሳየና እየመሰከረ ነው። "ሀገርና ሕዝብ እናጠፋለን እንጂ ስልጣናችንን አንለቅም" የአዋጁ ጥቅል ትርጉም። "መች ሀገር አዳናችሁና፣ መች ለሕዝብ ሕይወት*

ሳሳችሁና፣ መች ሰንደቃችንን አከበራችሁና፣ መች ታሪካችንን ጠበቃችሁና" ምላሻችን ሊሆን ይገባዋል።

***ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!***

በትንሹ ለአለፉት አርባ አመታት ተሰቃይተሃል። በደርግ ፋሽስታዊ አገዛዝ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ልጆችህን አጥተሃል። ልጆችህን በየቤትህ ደጃፍ ገድሎ "አካኪ ዘራፍ" ያለው ደርግ/ኢሠፓ ሊወድም፣ ሊቀበር የቻለው በትግልህ ነው። "እግዚኦ አምላክ! የአላህ!" ያሰኘው ደርግ በሚዘገንን መልኩ ትውልድ ቀብሮ ወደ ታሪክ አተላነት የተቀየረው በተግባሩ ነው። በሕዝብና በሀገር እየማለ እምዬ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለበታኝና ለከፋፋይ ዳርጓት አሽልቧል። ዛሬም የወያኔ/ህወሀት ወንበዴ አገዛዝ ጭፍጨፋን በአዋጅ ደንግጓል። በስምህ እየነገደ መግደሉን በይፋ አውጥቶታል። ወያኔ/ህወሀት በጓሮ በር የሚያፈሰውን ደም በፊት ለፊት ጀምሮታል። "ሕዝቡ በጠየቀን መሠረት ..." እያለ ሲዘባርቅ እራስህን እየናቀና ሊያወድምህ እንደተነሳ መስካሪ ነው። ሕዝብማ የጠየቀው "የወያኔን መውደም" ነው። ሕዝብማ የጠየቀው መብቱን ነው። ሕዝብማ የጠየቀው ነፃነቱን ነው። ሕዝብማ የጠየቀው ሚላስ ሚቀመስ ነው። ሕዝብማ የጠየቀው ሀገሩን ነው። ሕዝብማ የጠየቀው ***አረንጓዴ ቢጫ ቀይ*** ሰንደቅ ዓላማውን ነው። ሕዝብማ ያለው ልጆቼን ነው። ሕዝብማ ያለው ሃይማኖቴን ነው። ሕዝብማ ያለው ታሪኬን ነው። ሕዝብማ ያለው የራሴ መንግስት ነው። ሕዝብማ ያለው በቃኝ ወያኔ ነው።

አሁን ሀገራችንና ሕዝባችን ያለንበት ሁኔታ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ነው። ኢትዮጵያችንን የማዳን ሀገራዊ ግዳጅ ላይ ነን። ከወራሪና ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሀገራችንን ለመከላከልና የግዛት አንድነቷን ለማስከበር የፈሰሱ ደሞች ክብር ለኢትዮጵያ ነውና ሀገራችንን ለማዳን ማንኛውንም መስዋዕትነት መክፈል ይገባናል። ወያኔ የጅምላ ጭፍጨፋ ለማድረግ አቅዷል። ወያኔ ከአለፈ ታሪክ የተማረው ቢኖር የደርግን የጅምላ ጭፍጨፋ ነው። ዕድሜ፣ ሃይማኖት፣ ዘር፣ ፆታ ሳይለይ ደርግ በጅምላና በአዋጅ በሕዝብ ልጆች ላይ የፈጸመውን "ቀይ ሽብር" ወያኔ በሌላ መልኩ እየደገመው ይገኛል። ዛሬ እማንኛውም ቤት በተፈለገው ጊዜና ሰዓት እየተፈተሸ፣ እየተበረበረ፣ እየተዘረፈ ያስጉኛል ተብለው የተጠረጠሩም በጅምላ እየታፈሱ፣ እየተሰቃዩ፣ እየተገደሉ ነው። ኢትዮጵያችን ዳግም የደም መሬት እየሆነች ነው። ያለን ኃይልና ጥንካሬ አንድነታችን ነውና ወያኔ የረጨውን ዘረኝነት አስወግደን በጋራ ኢትዮጵያችንን እናድናት። ለኢትዮጵያችን መበታተን ከዘመናት በፊት ያለሙ ባዕዳን ኃይሎችን የመፍትሄአችን ምንጭ አናድርግ። አፍሪካን እንደፈለጉ ለመግዛት፣ ለመቦጥቦጥ የኢትዮጵያን አንድነት አይመኙም። ሀገራችን ብርቅዬ ትውልዱን ያጣችው በውጭ ኃይሎች የተቀነባበረ ሤራ መሆኑን አንዘንጋ። የዐድዋ ድል የጥቁር ሕዝቦች ድል ሆኖ ያስመዘገበው ታሪክ መጥፋትን ይመኛሉ፣ ኢትዮጵያችን በአንድነቷ ከቀጠለች ስጋት አለባቸውና በረቀቀ ዘዴአቸው ቦርቡረዋታል፣ ኢትዮጵያዊነት ስሜታችንን እየሸረሸሩ ይገኛሉና የማንነታችን መፍትሄ ቁልፉ ያለው በእጃችን ነው። ባህላችንንና ሃይማኖታችንን ተገን አድርገን የመጣብንን ሀገር በቀል ጠላት ሳንበረከክ ማሽመድመድና በድል አድራጊነት መወጣት ይኖርብናል።

***ውድ የኢትዮጵያ ወጣቶችና ተማሪዎች ሆይ!***

የ1960 ዎቹ ትውልድ ለሀገሩና ለሕዝቡ ቀና አመለካከት ቢኖረውም የከፈለው መስዋዕትነት እንደ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ድል ሳይሆን ፀፀት አስመዝግቦ አልፏል። ከያ ትውልድ ደካማና ጠንካራ ጎን ትምህርት በመውሰድ ኢትዮጵያችንን ለማዳን ከምንጊዜውም በላይ ግምባር ቀደም መሆን ይጠበቅባችኋል። ሁል ጊዜም የትግሉ መሪና ቀዳሚ ወጣቶችና ተማሪዎች ናችሁና ለሀገራችን

ቅደሙላት፣ ለሕዝባችን በደማችሁና በአጥንታችሁ ሕይወት ስጡት። በሀገራችን ላይ የመጣውን አስከፊ አደጋ እጅ በመስጠት ከመሞት ተጋፍጦ ድል ማድረግ ጀግንነት መሆኑን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" አበክረን እንገልፃለን። ለዚህም ለጠላት ባልተመቻቸ መልኩ መደራጀትና መሰባሰብ ይኖርብናል። እስከ አፍንጫው የታጠቀንና በአዋጅ ደረጃ "አጠፋለሁ! እደመስሳለሁ!" ያለን የወንበዴ ቡድን ለማሽመድመድ መደራጀትን ይጠይቃልና እራሳችሁን አደራጁ። ወያኔ ፋሽስታዊ ባህሪውን በይፋ አውጇል። ከእንግዲህ ለወያኔ መምበርከክ ማለት እየታነቁ መወርወር መሆኑን ግንዛቤ በመውሰድ "እምቢኝ ለሀገሬ! እምቢኝ ለሕዝቤ" ብላችሁ ተፋለሙ።

ወያኔ ዛሬ የሳይበር (ኢንተርኔት) አገልግሎትን፣ የፌስ ቡክ፣ ኢሜል፣ ቫይበር፣ የስልክ መገናኛዎችን ወዘተ ዘግቷል። ማንኛውንም ዓይነት እንቅስቃሴ ሰላማዊ ሰልፍ አይደለም ሁለትና ሦስት ሆኖ መገኘትን አግዷል። በአዲስ አበባ ትምህርት ለማስጀመር ፈርቷል። በጥቅሉ የወያኔ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሽንፈት ምልክት ነውና የተገኘውን ድል በድል ማስመዝገብ ይጠበቅብናልና የትግሉ ቀዳሚ ትሆኑ ዘንድ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ጥሪያችንን እናቀርባለን።

***ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!***

ወያኔ/ህወሀት ሰሞኑን በቴሌቪዥን መስኮት "ተሳስታችኋል፣ መታረም ይገባችኋል ወዘተ" እየተባለ በተሰባሰቡ ምሁራንና፣ የተለያዩ ፖለቲካ ድርጅት አባላት የሚሠራውን ወያኔአዊ ቲያትር ባለቤቱ እራስህ ነህና እንዳትታለል። የተጀመረውን ትግል ለማቀዝቀዝና ለማዘናጋት እየተካሄዱ ላሉ የወያኔ ቅስቀሳዎች እንዳትዘናጉ። ዛሬ ወያኔ የመጣበትን ሕዝባዊ ማዕበል እንደምንም አዳክሞ እንደለመደው በተናጠል እያነቀ ሊቀብርህ ተዘጋጅቷልና ዳግም እንዳትታለል። የ1997 ዓ.ም. ድልህን እንዴ አሽመድምደው በወያኔ ቀንበር ሥር እንደገና ለ11 ዓመታት እንድትማቅቅ የተደረገበት ስህተት በምንም መልኩ እንዳይደገም እራስህን ብቻ አድምጥ። ስለ ተሸከምከው መከራና ስቃይ ማንም ሊያስረዳህ አይችልምና በየቤትህ የደረሰው የ25 ዓመት ጉድና መከራ፣ የልጆችህ የግፍ ስቃይና ግድያ ምስክር አያሻህምና እናቶች፣ አባቶች፣ ሕፃናት፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ምህመናን፣ እስላሞች፣ ሠራተኞች፣ መምህራን ወዘተ በዘርና በአካባቢ ሳትከፋፈሉ በጋራ የወያኔን አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለወያኔ መቀበሪያ አድርጉለት። ሕዝባዊ አዋጅ አውጁበት። ኢትዮጵያችን በሉት። ሀገራችንን በሉት።

የወያኔ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መቀበሪያው ይሆናል!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"

ጥቅምት 14 ቀን 2009 ዓ.ም. (October 24, 2016)

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" በቅርቡ መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org

ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com